# የኤጀንሲው ሰራተኞች ከአገር መከላከያ ጎን እንደሚቆሙ አስታወቁ

ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ አመራርና ሰራተኞች "**ለአገር መከላከያ ክብር እቆማለሁ**" በሚል መሪ ቃል የተዘጋጀው አገር አቀፍ ፕሮግራምን ህዳር 8 ቀን 2013 ዓ.ም በደማቅ ሁኔታ አከበሩ፡፡ ፅንፈኛው የህውሃት ቡድን ጥቅምት 24 ቀን 2013 በሰሜን እዝ ላይ ያደረሰውን ጥቃት ተከትሎ መንግስት እየወሰደ ባለው ህግ የማስከበር እርምጃ የኤጀንሲው ሰራተኞች ከመንግስት ጎን መሆናቸውን የገለፁ ሲሆን በእለቱም የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ ለመከላከያ ደም መለገስ ለሚፈልጉ ጥሪ ባስተላለፉት መሰረት የኤጀንሲው ሰራተኞች ፍቃደኝነታቸውን በመግለፅ ላይ ይገኛሉ፡፡







# በከፍተኛ ቦታዎች የአየር ጠባይ ለውጥ ማጣጠሚያ ፕሮጀክት ከሚተገበሪባቸው ክልሎች ለተውጣጡ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ለሚቀጥሉት ለአራት ቀናት የሚቆይ ስልጠና ተሰጠ

ኤጀንሲው ከአካባቢ ደንና አየር ንብረት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በከፍተኛ ቦታዎች በኦሮሚያ (ያያ ጉለሌና ሰበታ ሀዋስ ወረዳዎች)፣ በአማራ(ደሴ ዙሪያና ደዋ ጨፋ ወረዳዎች)፣ በሲዳማ ሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ እንዲሁም በደቡብ ክልል አርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ የማጣጣሚያ ፕሮጀክቱ ከሚተገበርባቸው እያንዳንዱ ወረዳዎች አራት ዋና ዋና የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ማለትም ከግብርና፣ ከአካባቢ ጥበቃ፣ ውሃ፣ ጤናና የወረዳ አስተዳዳሪ ተወካዮችን ያሳተፈ ስልጠና መሆኑም ተገልፆል።

ስልጠናውን በንግግር የከፈቱት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ ኤጀንሲው ከአጭር፣ መካከለኛና ረጅም ጊዜ አንፃር የተለያየ ይዘት ያላቸው ቦታ ተኮር የትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎቶችን ለየወረዳዎቹ ሲሰጥ ቆይቷል። በእነዚህ ወረዳዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ባለፉት ዓመታት በተሰጡት ቦታ ተኮር ትንበያዎች ላይ ክትትል ስናደርግ በመቆየታችን በተለይም በአጠቃቀምና መረጃ አተረጎገም ላይ ክፍተቶች የተስተዋሉ መሆኑን አረጋግጠናል ብለዋል። በዚህም መሠረት ክፍተቱን ለመሙላትና የአካባቢውን ምርታማነት ለማሳደግ ዛሬን ጨምሮ ለሚቀጥሉት አራት ቀናት የሚቆይ ስልጠና ለመስጠት መታቀዱን ገልፀው የየወረዳ ተወካዮችም የሚሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ተረድታችሁ አገልግሎቱ በሚፈለገው ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ የአርሶ አደሩን ምርታማነት በማሳደግ በኩል ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ጠቅሰው፣ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንደሚወጡ

ያላቸውን እምነት በመግለፅ የመድረኩን መከፈት አብስረዋል። በኤጀንሲው የፕሮጀክቱ አስተባባሪ የሆኑት አቶ አሳምነው ተሾመ በእያንዳንዱ ወረዳ እንደየ አካባቢያቸው የዝናብ መጠንና ስርጭት፣ ዝናብ በብዛት የሚያገኙባቸው ወቅቶቻቸው ጭምር የሚለያይ መሆኑንና ለእያንዳንዱ ወረዳ የረጅም ዓመታት የአየር ጠባይ ፕሮፋይል ማለትም የወቅት ዝናብ አጀማመርና አወጣጥ፣ መጠንና ስርጭት፣ ከፍተኛና ዝቅተኛ የአካባቢው ሙቀት መጠን፣ አካባቢው ለምን ዓይነት አዝዕርት እንደሚመች ለማወቅና የሰብል መረጣ ለማካሄድ ብሎም የማሳ ዝግጅትና የአጨዳ ጊዜን ለመወሰን የሚያስችሉ መረጃዎች በፕሮጀክቱ አማካኝነት መዘጋጀታቸውና ሲሰጡ መቆየታቸውን ገልፃዋል።

በአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ኮሚሽን የፕሮጀክቱ አስተባባሪ የሆኑት አቶ ተስፋዬ ወልደየስ ባለፉት ዓመታት ለፕሮጀክቱ ስኬት ከኤጀንሲው ጋር በርካታ ሥራዎችን ሲያከናውኑ መቆየታቸውን ገልፀዋል።







# ኤጀንሲው የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ላይ ዳግም የማጣራት ሥራን አከናወነ

ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ለፕላን ኮሚሽን ቀደም ብሎ በላከው የዓሥር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ (2013-2022) ላይ ከኮሚሽኑ ማስተካከያ እንዲደረግ በተላከው ገብረ -መልስ መሠረት የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎችን በሳተፈ መልኩ ከኅዳር 10 እስከ 11 ቀን 2013 ድረስ ሲያከናውን የቆየውን ሥራ ዛሬ አጠናቀቀ።

የኤጀንሲው ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ክንፈ ኃ/ማሪያም በኮሚሽኑ የተሰጠውን ግብረ- መልስ ለኃላፊዎቹ በዝርዝር አቅርበዋል።

ይሄንን ተከትሎ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል የተሰጠውን ግብረ-መልስ መሠረት በማድረግ የሚመለከተውን ዕቅድ እንዲከልስና እንደየ ሥራ ባህሪያቸው በተደራጀው ቡድን ከነ ማስፈፃሚያ በጀቱ በማቅረብና በማስተቸት የተስማሙበት ለጋራ መድረክ በአዳማ ከተማ ደንበል ቪው ሆቴል እንዲቀርብ ማሳሰቢያ በሰጡት መሠረት በየተወካዮቻቸው በኩል ለጋራ መድረክ እንዲቀርብ ተደርጓል።







# ከክልል ማዕከላት ኃላፊዎችን ጨምሮ 3 ባላሞያዎችን ያሳተፈ የስልጠነና የግምገማ መድረክ ተካሄደ

በስልጠናው የተሳተፉት ኃላፊ፣ የሰው ሀብትና የለውጥ ባላሞያዎች ሲሆኑ ስልጠናውም ያተኮረው በተሻሻለው የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ መመሪያ፣ የመንግስት ሠራተኞች ዲሲፕሊን አፈፃፀም ዙሪያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችል ስልጠና እንዲሁም በፎርም አሞላል ጭምር ላይ መሆኑ ታውቋል።

ስልጠናውን የሰጡት በኤጀንሲው ከፍተኛ የህግ ባለሞያና የስነምግባር መኮንን ተወካይ የሆኑት አቶ ታደሰ ጪምዲ ናቸው።

የመድረኩ ተሳታፊዎች ኅዳር 8 ከጠዋቱ 5:30 በመቆምና በማጨብጨብ ለመከላከያ ሠራዊታችን ያላቸውን ክብርና ድጋፍ አሳይተዋል። በተጨማሪም እያንዳንዱ ማዕከላት የየራሳቸውን ዕቅድ አፈፃፀም እንዲያቀርቡ በማድረግ የማዕከላት የ3 ወር ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ተከናውኗል።



